# 'ያ ሐመልማል' - ዳሰሳ

Anteneh Aklilu

*"…ራቋን አየኋት ምድረ-በዳ ቆማ*
*የተጨነቀች ነፍስ ሥጋዋ ሆኖባት አሮጌ ባድማ…"*

በተሰኘው የዮሓንስ አድማሱ ሁለት ስንኞች የሚጀምረው ይህ ጥበባዊ ደረጃው ከፍ ያለ አጭር ልቦለድ በአንደኛ መደብ ነጠላ የትረካ ዘዴ የአንዲትን ባሏ የሞተባት ወ/ሮ የሰቀቀን ፤የፀፀትና የቁጭት የህይወቷን ጉልህ አጥፋቶች በመብሰክሰክ የምታነበንብበትን የነፍስ ሲቃ አንጠፍጥሮ ይዟል፡፡

ደራሲ አዳም ረታ ከባህርያቶቹ ዙሪያና ውጪ ሳይሆን የሥነ ልቦናቸውን ውኾንብርና ጥልቀት በዝርዝር ማድመጥና ማስደመጥ የተካነ ምትክ አልባ የጥበብ ሰው ነው፡፡ በገጸ- ባህርያቱ ጊዜና ቦታ ውስጥ በጥበብ መንፈስ ሃይል እየተገኘ ከደቂቅ የስሜታቸው ቀለም እስከ ጉልህ የሕይወታቸው ኢጋጣሚ ድረስ በልቦናው ጀሮ ሀሴትና ሲቃቸውን የሚያደምጥ፤ አድማጦም ፍጹም ምትሃት በሆነ አገላለጽ ሁላንተናቸውን የሚያብራራ እፀብ ደራሲ ነው፡፡

አዳም ረታ በቁጥር ብዙ የሆኑ አጫጭር ልቦለዶቹን በተለያዩ መድብሎች ሰብስቦ ያደረሰን መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሁሉም ፈጠራዎቹ ተዋጥተውለታል፡፡ ያ ሀመልመል የሚለው የነፍሱ ድርሳን ግን ይለያል፤ አዳምረታ ፆታ አልባ በሆነችው ጥበባዊ ነፍሱ በሥጋ ከሚወክለው ወንድ መሆኑ ማዶ ተሻግሮ ለቅጽበት እንስታይ ሆኖ የከተባት ልዕለ- ፈጠራው ናት፡፡ ያ ሐመልማል፡፡ አዳም ረታ ይቺን ልቦለድ ሲጽፍ በእርግጠኝነት ሴት ሆኖ ነው፡፡ አለበለዚያ እንደዚህ አይዋጣም.... አለበለዚያ....

ያ ሐመልማል በሃያ ገፆች (251-270) ውስጥ ቅልብጭ ተደርጋ የተንቆረቆረች የነፍስ እንጉርጉሮ ናት:: የአንዲት እንስት መንፈስ በሃዘን ባህር ተዘፍቃ የወረደችው የዓመታት ሙሾ፡፡ ፀፀት፤ ቁጭት፤ ባዶነትና ቀቢፀ ተስፋ በወለደው ትዝታ የተነበነበች መረር ትካዜ፡፡ ያ ሃመልማል!!

ባለታሪኳ ዮዲት ትባላለች፡፡ ከአጠቃላይ የታሪኳ ስሜት ጉልህነት አንፃር ስሟን ልብ አንለውም፡፡ በገጽ 264 ላይ አንድ ጊዜ ተወዳጅ ባለቤቷ ሲጠራት ስሟን ላፍታ እንሰማዋለን እንጂ ከዚህ ባለፈ ስሟ ትርጉም የለውም፡፡ መጠሪያ ስያሜ ባይኖራትምንኳ የፈጠራው ጥረት አይጓደልም፡፡ የልቦለዱ ውበትም ሆነ ህቅ ያለው በትዝታዋና አሁን ባላት ውስጣዊ ማንነቷ መሀከል በሚገለጠው ህልውናዋ ላይ የምትነግረን ሰቀቀኗ ውስጥ ነው፡፡ ባህሪዋ ነፍሷ ካስተናገደው ረቂቅ ብሶት ውስጥ እንደመጣላት እየቆነፀለች በምታወጋን መራር ገጠመኞቿ ከልባችን ዘልቃ ትታተማለች.......

በየቅጽበቱ በሚገጥሟት የህይወት ዕጣዋ ውስጥ ተገኝታ ፍጹሞ ታማኝና ግልጽ በሆነ መንፈስ የወሰደቻቸውን አጻፋዎች ስሜት እየነገረችን ውሎ አድሮ ከገጠማት እውነት አንፃር ራሷንና ህይወትን እየታዘበች ርቃን ነፍሷን ትገልጥልናለች፡፡

ዮዲት ዛሬ ላይ የሰቀቀን ቆማ ለዚህ ህይወቷ መንስኤ የሆናትን የስህተቷን ድርጊት አስራ ሁለትና አስራ ሦስት አመታት ወደኋላ እየተሳበች መልካም የነበረውን ወድ የፍቅርና ትዳር ዘመኗን ጣዕም የቁጭት ታስቃኘናለች፡፡ በሁለት የስሜት ዋልታዎች ጫፍ ተፃንፋ የቆመችው ይህቺ ነፍስ፤ በትላንቷና በዛሬዋ እርሷነቷ መሃከል የተፈጠረውን ገደብ አልባ የስሜት ገደል፤ የመሪር ህይወቷን ጥቂት አንጓዎች  እያነሳች ጥልቀትና ግዝፈቱን ትስልልናለች ፡፡

ያቺ ጥቂቶች ብቻ የሚታደሉትን ባፈቀሩት ተፈቅሮ በፍቅር አብሮ ለመኖር የታደለችና፤ ብዙዎች የማይገጥማቸውን ከእውነተኛ ፍቅር ባሻገር በተድላና በምቶች ተንደላቃ የህይወትን የበራ ፊት ብቻ ትመለከት የነበረችው ዮዲት፤ ህይወት በውድ ባለቤቷ ምንተስኖት በኩል ዕለት ዕለት የበረከተና የፍቅር ቱሩፋቶቿን እጆች የዘረጋችላት ዮዲት፤ ዕድል የሰጠቻትን ረድዔት ልብ አላለችምና ተዘናጋች...... የፍቅርና የተድላ ህይወቷን ብርቅ መሆን አጥታው ዋጋውን አላወቀችውምና ሳተች.....ገጽ 252 -254፡-

“.....አንገቴንም ለማባበል ከህብሌ ጋር በሰፊ እርጥብ አፉ ይይዘዋል፡፡ ዘፈን አይችልም ግን በሻካራ ድምጽ ላንጎራጉር ሲል አንጀቴ ይላወሳል፡፡ ታላቅ ደስታና የምቾች ጊዜ ነበር....ስህተቱ ይኼ ሳይሆን ይቀራል?.. ስህተቴን ሁሉ በመወደድ እየሰረዘ ሲቀበለኝ ጊዜ ጥጋብ የተባለው ነገር ተሰምቶኝ....(ገጽ 252)

.”.....አንዳንዴ ስንወደድ ስንለመን ለፍቅር ድሪያ በሚወደን ስንጓጎጥ በትንሹ በመግደርደር ይህን መለመን፤ ይህን ልምምጥ፤ ባጉል መልከ እንድንሰማው እንፈልጋለን....” (ገጽ 254)

እናም ዮዲት በህይወት እያለ  ዋጋውን ልብ ሳትለው  ባሏን በሞት ተነጠቀች፡፡ ፍቅሯን ለዘለዓለም አጣቸው፡ ፡ ከጥቂት ወድ የትዳር አመታት ቆይታ በኋላ ምንተስኖት ተለያት፡፡ ያ ከቻለ ያለቸውን ሁሉ የሚያደርግላት ፍቅሯ፤ አንድ ነገር ብቻ ጠይቋት ያንን ሳታደርግለት እንዳዘነ መኪና በላው .........ገጽ 257፡-

“... አልመጣም ፡፡ ለዘለአለም አልመጣም፡፡ የተቀመጠበት ታክሲ ከአንድ አንቡላንስ ጋር ተጋጭቶ ነው አሉ፡ ፡ ከአንቡላንስ ጋር፡፡ ከሁለት ሰዓት በኋላ ሆስፒታል ተጠርቼ ሄድኩና ሲሞት አየሁት፡፡ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ..... (ገጽ 257)

ተመልካችና ታዛቢ በሚጎመጀው የተንደላቀቀ ቪላ ውስጥ ብቻዋን ቀርታ፤ በቂ ደሞዝ በሚያስገኝ መስሪያ ቤት ተቀጥራ እየሰራች፤ ውጪያዊ ተክለ- ስብዕናዊ ተመችቶት እየታየ፤ አገር እየቀናበት እርሷ ግን ውስጧ በሰቀቀን እሳት  አለቀ፡፡ (ገጽ 260)

“....በዓለም ላይ አንድ ሰው ብቻ ተወዶ ያው አንድ ሰው ሲሞት

ምን ይደርጋል  ቤት ብቻውን ምን ትርጉም አለው?...”(ገጽ 252)

የዮዲትን ሃዘን ፍፃሜ አልባ አድርጎ ተከታትለው በነጎዱት ጊዜያት ሀኪምነት የውስጧ የፀፀት ቁስል ያልተፈወሰበት ምክንያት፤ ውድ ባለቤቷ የተማፀናትን አንድ ብቸኛ ውለታ አለመፈፀሟ ብቻ አልነበረም፡፡ ፍቅረኛዋ እንድታደርገው ሰግዶ የለመናት ያድርጊት ተፈጥሮ ራሷ መርቃ የሰጠቻት የህይወት ትርጉምና ልምላሜዋም መሆኑ ጭምር ነው፡፡ ቪላ ቤቷን በአረንጓዴ ልምላሜያቸው መልሰው መልሰው የሚያስውቡት የግቢዋ ሀመልማሎች የሴትነት ጸጋዋን ንጥፈት በንጽጽር ሲገልጡላት ዮዲት እንደተሸወደች ገባት ፡፡

"...እዚህ ሳሎኔ ተቀምጬ ወደ ውጪ ስመለከት.... የእኔ ህይወት አጠወላለጉ እስኪያስደነግጠኝ እስኪያሳብደኝ ድረስ ተዘበራርቆና ወድቆ ሳለ፤ እዚች አጥሬ ዙሪያ የተንጣለለው የሃረግ አመልማሎ ግን አማረም አላማረም ሳያቋርጥ መድመቁ መተንፈሱ ይገርመኛል፡፡.....( ገፅ 258)

ወይም....

" ..የዚህ የአትክልት ቦታ በየወቅቱ መለዋወጥ ያስቀናል፡፡ እንዲህ ሁኚልኝ ነበር ያለኝ እኮ፡፡ እንዲህ አብቢ እንዲህ አፍሪ ነበር ያለኝ ፡፡ ተፈጥሮ ሁኚ ነበር ያለኝ፡፡ እሱን አጭር አሳቢ እኔን ግን ብልህ አደረኩ...."(ገጽ 259)

ወይም ...

' .... በጊዜ ብዛት እየወፈረ ....የመነኮሰ ጭኔ ብቻውን እያደገ፤ የወር አበባዬ እየመጣ ሲጠፋ፤ ጡቴ እየወደቀ የሆዴ ቦርጭ እየገፋ ሽንጤ እያጠረ ሲመጣ አያለሁ....መታጠቢያ ቤት መስተዋት ፊት ለፊት ቆሜ የብቸኝነት አወዳደቄን ሳይ ወተት ሳይወርደኝ፤እንግዴልጅ ሳይጠረገኝ፤ ማህጸኔ ሳይቆስል፤ ለአንድ ለምወደው ሰው ይህን ሁሉ ስጋና ደም ስር ሳልሰጠው መቅረቴ አንጀቴን ይበላኝና ከቆምኩበት ወድቄ መሬት እየመታሁ አለቅሳለሁ ... " (ገፅ 260)

ወይም ...

" ..... 'ውለጅልኝና እርጅና ይውረረኝ...' ይለኛል ፡፡ ይለምነኛል፡፡ እግሮቼ መሃል ተደፍቶ አብራኬን እንደ ውሻ እያሸተተ ይለምነኛል፡፡ራሴ አዋቂ የሆነኩ መሰለኝ ፡፡ ይመስላል...ሲመች ሲመች ሰው አዋቂ የሆነ ይመስለዋል፡፡ ሁላችን ታይታኒክ ነን ያቺ ጀልባ፡፡ ባህር ላይ ሳይሆን ቂልነት ላይ እንደ ቆመች ያልገባት፡፡ ብረታ ብረቶች ቀናቸው ያልሆነ ዕለት ከደንከል ይደክማሉ... " (ገፅ 266)

ታዲያ ዮዲት ዞሮ ዞሮ ያው ሰው ናትና በሞት የተለየ ባለቤቷን እጦት ለመተካት ልዋጭ ፍለጋ መማተርዋ አልቀረም፡፡ዳኑ ምን ያደርጋል..... ዓለም ከ6 ቢሊዮን ሴቶችና ከአንድ ወንድ ብቻ የተሰራች ነበረችና (262) በፀፀትና በበደል ቆስላ ከፍለጋዋ ለዘለዓለም ተገታች፡፡

"......ምንተስኖት በፍቅር ጠቅልሎ ያየውን ነገር እነርሱ ያለፍቅር ሊወስዱት ይሞክራሉ ፡፡ የሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ እንጂ ማንም አይደሉም። ከኔ ያማሩ ሴቶች እንደከብት ሊያንጋጉ ይችላሉ፡፡ ሁለመናዬን ለማየት ምንተስኖትን መሆን አላባቸው። አይገባቸውም የክብር ትርጉም አይገባቸውም፡፡ምንተስኖት ሲጠፋብኝ የጠፋብኝ ከእንጦጦ ንፋስ ስልክ፤ ከአየር ጤና ኮተቤ የተዘረጋው የአዲስ አበባ ሽርሙጥና አይደለም የጠፋብኝ ፍቅር ነው ....(ገፅ 265)

የዚህ ልቦለድ ስራ ምጥቀትና ረቂቅነት ኃይለ ቃሉ ያለው ከዚህ ፍለጋዋ መኮላሸት በኋላ ዮዲት በሚሰማትና በምትሆነው መራራ የህይወት ዕውነታ ላይ ነው፡፡ የጥበቡ አስደማሚነት ይህ ነጥቡ ነው፡፡ ያቺ ፍቅርኛዋን ከማሪያም የተጋራች ጽንፍ የላሸ አፍቃሪ ገጽ (264)

“......ግድግዳ አስጠግቶ የውሽቴን እየተንፈራፈርኩ ድቡልቡል እጁ ወገቤን ጨምድዶኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ስል ሊስመኝ አፉ እየተንሳፈፈ ሲመጣ ከለበኑ ውስጥ ካፉ ምራቅ የረጠበ ሽፍ ያሉ ጥቁር ነጠብጣቦች አየሁ ፡ ፡ ቀስ እያለ ስለሚጠጋኝ በፍጥነት ቆጠርኳቸው፡፡ ስድስት፤ ስድስት ማርያም የሳመቻቸው ነጠብጣቦች ፤ ከንፈሮቼን እርሱ ነክሶ እኔ ግን በህሊናዬ ምን ቢቆርጣት ነው ማርያም ፍቅረኛዬን የነካችብኝ አልኩ፡፡ ደግሞም ኮርቻለሁ፡፡ እንደ እኔ ፍቅራቸውን ከማርያም የሚጋሩ እነማናቸው ...... (ገፅ 264)

ያቺ በባለቤቷ ፍቅር ሰጥማ ሁሉም እንስቶች የሚጓጓለትን ልጅ መውለድ ጭምር የባለቤቷን መውደድ እንዳይሻማት መስዋዕት ያደርገች ወጣት .....

“ .... ልጅ መውለድ ከእኔ ይልቅ እሱ ይፈልጋል ብዙ ጊዜ ባይሆንም ደጋግማሞ ልጅ መውለድን፤ ልጅ መልካም ነገር መሆኑን ያነሳሳል እኔ ግን ልጅ ማርገዝና ማጥባት አልፈለኩም ... እሱን ባሌን ብቻ ነበር የፈለኩት ከሁሉ ነገር እሱ ይበልጥብኝ ነበር...”(ገጽ 253)

ያቺ በህይወት ተመልሶ የማይመጣ ባሏን ህያው ፍቅር በነፍሷ ተሸክማ ለሌላ ወንድ መሸነፍ ያቃታት ህያው አፍቃሪ .....
(ገጽ 263)

“..... ከዚህ ከኢዮኤል ጋር ስንገናኝ አላማዬ ለማምለጥ እንጂ ተመልሼ በከፊል ምንተስኖት፤በከፊል ግን እንደ ወሲብ ዕቃ ወደሚቆጥረኝ ሰው ለመምጣት አልነበረም፡፡ ጠፋሁበት፡፡ቢያስፈልግ ጠፋሁ፡፡ ጠዋት ጠዋት እዚህ ብሄራዊ ትአትር ስራ ሲገባና ሲወጣ አየዋለሁ፡፡ ድርጊቱ ያሳዝነኛል፡፡እሱም ያሳዝነኛል፡፡ ግን ምን ላድርግ .....” (ገጽ 265)

ያቺን ምስኪን...ያቺን ሀዘንተኛ.... አንድ ዕለት ፀፀት ፤ስቀቀን፤ ሀዘን፤ ብቸኝነትና የጊዜ ስልጣን ተደራርበው በውድቅት ከቤቷአስወጥተው አውላላ ላይ ጣሏት፤ የተከበረ የታፈረና የተፈራ ግርማዋን ገሰው ርቃን ነፍሷን መንገድ ዳር አሰጧት ...

“.....ሰዓቴን አየሁ

ከምሽቱ 5፡06 ሰዓት

ልብሴን አውልቄ አዲስ የገዛሁትን ውስጥ ልብስና ሌላ አዲስ አጠር ያለ ቀሚስ ደርቤ ጫማዬን ለውጬ፤ ፀጉሬን አስተካክዬ በፍጥነት ከቤቴ ወጣሁ ....” ( ገጽ 267)

የተራበ ነፍሷ ጨለማውን ሰንጥቆ ሰው ፍለጋ ወጣ ፡፡እርሱም አልሆነ፡፡ ዮዲት ብቻዋን በደረቅ ሌሊት ባዶ ጎዳና ላይ እንኳን ሰው እንስሳ እየናፈቀች....

“........ አዲስ አበባ የአውሬዎች መኖሪያ የለም እንጂ .... በዚህ ሰዓት ከዝንጀሮ ብድቅል እወዳለሁ፡፡ ባልታወቀ ባልተፈለገ ባልተደነቀ ባልተፈቀረ የሰው ወንድ ልጅና በእንስሳነቱ ከእንስት ዘሩ የሚማሰል የሴትነት ጠረኔ ጎትቶት በምወልድለት ወንዴ ዝንጀሮ መካከል ልዩነቱ ምንድን ነው ፍቅር ከሌላ ምን የቀረ አለ?” (ገጽ 268)

መቼም የዮዲት ነፍስ ተንገብግባ በንናለችና በድን ርቃን ህልውናዋን ጨብጣ እልፍኟ ገባች፡፡ ዮዲት ከዚህ ባለፈ የሚመዘገብ ታሪክ የላትም፡፡ ዮዲት አልቃለች፡፡ ደራሲው የዚችን መከረኛ ነፍስ ውሎና አዳር ከዚህ ምሽት ባሻገር ምንም ነገር አላቀብለንም፡፡ገፀባህሪዋ ተብስክስካ፤ ተንገብግባ፤ተንጠፍጥፋ፤ አልቃለችና ቀሪ ወግ የላትም፡፡ ከዚች አፍታ በኋላ ማንም አካል በተፈለገው ታምር ቢያንቀርቅባት ከዮዲት ህይወት ውስጥ ጠብ የሚል የህያውነት ስሜት አያገኝም፡፡ የዮዲት ሰማይ አይነጋም፤ የዮዲት ምድር አይወግግም፡፡ ዮዲት በቁሟ ለዘለቄታው የጠለቀች ጀንበር ሆናለች፡፡

"......በቀስታ እየተራመድኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ፡፡ ልብሴን አወላልቄ በውስጥ ልብስ የለመድኩት ሶፋ ላይ ተቀምጬወደምሽቱ፤ወደአጥሩ፤ ወደ ጎዳናው ፤ወደ ሚያስኮርፈው ሌሊት ማፍጠጥ ጀመርኩ፡፡ ዓለማ ያላቸው ግን ቃታ መሳቢያ ጣትያጡ እነዚህ አይኖች፡፡ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆነ፡፡... ሶፋዬ ላይ አንገቴን ሰብሬተኛሁ ....... እንደበቃው... ሁለቱ እግሮቼን ሶፋው መሀል ያለው ጠረጴዛ ላይ ስቅዬ ውስጤ እየበረደኝ.... ቅዥቴ መጣ አሁን ሞንተስኖት አይደለም ፡፡ አሁን ያ አትክልቱ ነው ያ አረንጓዴ ...ከዳርዳር አጥሩ ዙሪያ ያለው እግር እንዳበቀለ ሁሉ.... ወደ አንድ ትልቅ ሃመልማል ወደ አረንጓዴ ጃርት የመሳሰለ ኳስ ተለውጦ እየተንፏቀቀ መጥቶ መስኮት ዳር ከውጪ ቆሞ እንደ ሰው አየኝ....ከላዩ ላይ ጭራሮ ብቻ.... ቤቱን በጉልበቱ ንዶ ሲገባ መስተዋቱ ያለድምጽ እንደ ላውንደሪ ላስቲክ እየተጣጠፈና ያያዙት ብረቶች እንደ ቅቤ ዘንግ እየቀለጡ.... የጠወለገው ሀረግም ጠረጴዛ ላይ እየተሳ በሰውነቴ ላይ በሚቧጥጡ ወፍራም እግሮቹ እየወጣብኝ ... ከዚያ በእግሮቼ መሀል ሙቀት ፈልጎ እንደ እባብ እየተነፈሰ ማህፀኔ ውስጥ ሲገባ ደረቅነቱ ሲገባ....
ከቅዥቴ እተንቀጠቀጥኩ በላብ ተዘፍቄ ባነንኩ....ጭኖቼ ልክ በእሾህ እንደተጠቀጠቁ ሁሉ እየጠዘጠዙኝ የቀረችው በሰውነቴ ወጣትነት ተማምና የቆመችው ተስፋ፣ልቤ ላይ በታላቅ ድምጽ/ ጩኸት ስትውድቅ እሰማታለሁ፡፡..... ልክ ግርርር ብላ ከንፏን እያማታች ዘልቃ መብርር እንዳቃታት ወፍ..... በጉጉት ወደ ሚጠብቃት የዘመን አወሬ አፍ... በቀዝቃዛ ሳሎኔ ውስጥ በቀዝቃዛ ሌሊት ከቀዝቃዛ ሰውነት..... ጣውላ ካረገዘ ሰውነቴ ዕንባ መውጣት ጀመረ፡፡
ማልቀስ ጀመርኩ ....."(ገጽ 269-70)

ደራሲ አዳም ረታ ይችን ልቦለድ እዚህ ላይ ፈጽሚታል ፡፡ እኔስ ብሆን ከዚህ ወዲያ ምን እጨምራለሁ !? አበቃሁ!!

***

# የተጠቀሱት ገፆች (አለንጋና ምስር)በመጀመሪያው ህትመት (2001 ዓ.ም)አቀማመጥ መሰረት ነው ፡፡